# በኦሺንያ የኢህአፓ 36ኛ አመት በአል ተከብሮ ዋለ።

በአውስትራሊያ አህጉር፤ በሜልበርን ከተማ በተደረገው ዝግጅት፣ ከተለያዩ ከተሞችና ክልሎች የመጡ አባላት እንዲሁም በከተማው የሚገኙ አባላት፣ ደጋፊዎችና ጥሪ የተደረገላቸው ኢትዮጵያውያን በተገኙበት፣ በ September 7 2008 ቀን በአሉ ተከብሮ ውሏል።

ስብሰባው ፤ ለወደቁት ሰማእታት ጓዶች ማስታወሻ የህሊና ጸሎት በማድረግ የተጀመረ ሲሆን፤ ቀጥሎም፣ የአውስትራሊያ ሀገራዊ አመራር ኮሚቴ አባላትና የከፍተኛ አመራር ኮሚቴ አባል፤ በዚሁ በአል ለተገኙት ታዳሚዎች፤ ስለ በአሉ ምንነት ፣ ስለወቅቱ የኢትዮጵያ ትጨባጭ ሁኔታ ፣ የኢህአፓን አቋሞችና ፖሊሲዎች አስመልክቶ ሰፊ ገልጻ በመስጠት ከአድማጮች ለቀረቡት ጥያቄዎችም መልስና ማብራሪያ በማከል በጥሩ ሁኔታ ውይይቱን አካሂደዋል።

በዚሁ በአል ከተለያዩ ክፍለ አለማት፣ የኢህአፓ አካላትና አባላት እንዲሁም ከሀገር ቤት የተላኩት የድጋፍ መግለጫዎች ተነበዋል። የግጥሞችና ቀስቃሽ መዝሙሮች ቅንብርም በአሉን አድምቀውት ውለዋል።

ከተገኙት ታዳሚዎች በኩል አበረታች ድጋፍና የትብብር መንፈስ የተገለጸ ሲሆን፤ ድርጅቱንና ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ ሬድዮንንም ለመደገፍ፤ ያላቸውን ፍላጎት በአጽንኦት ገለጸዋል። ለወደፊቱም፤ በአውስትራሊያ የተለያዩ ከተሞችና ክልሎች፣ ይህ አይነቱ ድርጅታዊ እንቅስቃሴ እንደሚቀጥል በመግልጽ በጥሩ የአንድነት ስሜትና የትግል መንፈስ ከቀኑ በሁለት ሰአት የተጀመረው ስብሰባ ከምሽቱ ስድስት ሰአት ተፈጽሟል።

በኒውዚላንድም እንዲሁ በኦክላንድ ከተማ ፤ በዚሁ ቀን በተመሳሳይ ሁኔታ በአካባቢው የሚገኙ አባላትና የኢህአፓ ደጋፊዎች በተገኙበት በአሉ ትከብሮ ውሏል።
በሁለቱም የኦሺኒያ ክልሎች የሚገኙት አባላትና ደጋፊዎች ለውደቁት ሰማእታት ጓዶችና ህውልታቸው ለሆነው ድርጅታቸው ኢህአፓ ያላቸውን ታማኝነት ፤ እንዲሁም፣ ለጎስቋላው ህዝባችንና ለሃገራችን ኢትዮጵያ የማይናወጥ ቁርጠኛ የትግል አቋም አጽንተው፤ ትግሉን እስከመጨረሻው ለመቀጠል ቃልኪዳናቸውን በድጋሚ በማደስ ፤ በአሉን ደምድመዋል።

ድሉ የኢትዮጵያ ህዝብ ነው!
ኢህአፓ ያቸንፋል!

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com